# በጨለማ ላይ የገደል ጥላ

## ይኄይስ እውነቱ

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወታደራዊው የደርግ አገዛዝ ላይ በነበረው ሥር የሰደደ ጥላቻና ምሬት የተነሳ ለውጥ አጥብቆ በመፈለጉ፤ በአንፃሩም የወያኔዎችን የጫካ አጀንዳ ባለማወቁና ዕድል ሰጥተን እንያቸው በሚል ተስፋ በማድረጉ፤ ጥፋትን ሁሉ ምን ቀረን በማለት ንቅስ አድርገው በሚፈጽሙ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት ተይዞ ደኅንነቱ እና የአገራችን ህልውና (በታሪኳ ተወዳዳሪነት በሌለውና በከፋ መልኩ) አደጋ ላይ ወድቀዋል፡፡ ብርሃን ነፃነትን፣ ብርሃን እኩልነትን፣ ብርሃን የሕግ የበላይነትን፣ ብርሃን ብልጽግናን፣ ብርሃን ዲሞክራሲን ሲናፍቅ የነበረ ሕዝብ ለጨለማ ባርነት፣ ለጨለማ ዘረኝነት፣ ለጨለማ ፍትሕ አልባነት፣ ለጨለማ ችጋር፣ ለጨለማ ወንበዴዎች አገዛዝ ተዳርጓል፡፡ ይህ ወሮበሎች የሰለጠኑበት ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያለ ጥርጥር የጨለማው ዘመን ተብሎ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

ይህንን የመሠሪዎች አገዛዝ በሰላማዊም ሆነ በትጥቅ ትግል ለማስወገድ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካና የሲቪክ ማኅበራት እንዲሁም ግለሰቦች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በአሸባሪው ሥርዓት የለየለት ጭካኔና ድንቁርና፣ አጋር በሆኑት አሸከሮቹ ቅጥረኝነትና ሆዳምነት ባንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ተቀናቃኝ ድርጅቶች በውስጣቸውም ሆነ ከሌሎች ጋር ኅብረት ማጣት፣ በአንዳንዶችም ዘንድ የዓላማ ስንኩልነትና አርቆ አስተዋይነት ጉድለት፣ እንዲሁም የጥቂቶች ተልእኮ በውል አለመታወቅ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት 25 ዓመታት በማያቋርጥ ስቃይና እንግልት ውስጥ ይገኛል፡፡ ለቀጣዩም ዋስትና የለውም፡፡

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ሲያስተምሩ በጨለማ ላይ የገደል ወይም የዛፍ ጥላ ሲጨመርበት ጨለማው ጽኑዕ ይሆናል ይላሉ፡፡ ለዛሬ ጽሑፌ መነሻ የሆነኝ የጨለማውን አገዛዝ እንታገላለን በሚሉ ተቀናቃኞች ዘንድ (በተለይም በውጭ በሚንቀሳቀሱት) የሚታየው ልዩነት፣ እሰጥ አገባ እና ፑስሚያ ጨለማውን የሚያጸና የገደል ጥላ እንዳይሆን ያደረብኝ ሥጋት ነው፡፡ ሥጋቴ መሠረት አልባ እንዲሆን አጥብቄ እመኛለሁ እጸልይማለሁ፡፡

በቅድሚያ በዚህ ጽሑፍ የቀረበው አስተያየት በአመዛኙ ጥቂቶችን የሚመለከት፣ ከነርሱም ውስጥ በአመራር የሚገኙ፣ ምናልባትም በሕዝብ ደም ሥልጣን ላይ ለመፈናጠጥ የቋመጡ ወይም እኔ ባልበላው ጭሬ ልበትነው እንዳለችው እንስሳ ለእኛ ካልሆነ እናውክ የሚሉ ወይም የሌሎች መጠቀሚያ በመሆን በጉዳይ አስፈጻሚነት የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች/ግለሰቦች እና እነሱ ያፈሯቸው ተከታዮች አቋም ይመስለኛል፡፡ ይህን የእኔን ሥጋት የሚጋሩ ወገኖች በተቃዋሚ ስም ከተሰለፉ ነገር ግን አፍራሽ ተልእኮ ስላላቸው አንዳንድ ግለሰቦች/ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ በነፃው የብዙኃን መገናኛ አስተያየታቸውን አቅርበው አንብቤአለሁ፡፡ በመሆኑም ሁሉም በወል የሚጋሩአቸው ጉዳዮች በአለፍ ገደም የተነሳ ቢሆንም፣ አስተያየቱ ሁሉንም ተቀናቃኝ የፖለቲካ ድርጅቶች በጅምላ የሚመለከት ተደርጎ እንዳይወሰድብኝ ከብርቱ ማስጠንቀቂያና አክብሮት ጋር ለመግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

በመሠረቱ ተቀናቃኝ የፖለቲካ ማኅበራት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በሚደረገው ትግል ስልታዊ አንድነት ለመፍጠር ሲባል መለስተኛ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ለመድረስ የሚያደርጉት ወይይትና የሚፈጥሩት ኅብረት በጣም የሚደገፍ ሃሳብ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚደረገው ጅምር ለወደፊቱ አንኳር በሆኑ አገራዊ አጀንዳዎችና የልዩነት አቋሞች ላይ በሠለጠነ መልኩ ለመነጋገርና ተባብሮ ለመሥራት መንገድ ከፋች እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ይህ ዓይነቱ መድረክ ለእንኪያ ሰላንቲያ፣ ልዩነትንና አለመተማመንን ይበልጥ ለማስፋት ከዋለ ግን ተጠቃሚው ያለጥርጥር ወያኔ ይሆናል፡፡

ለዛሬው አስተያየት መነሻ የሆነኝ ለነፃነት ስልታዊ አንድነት በሚል በአሜሪካ ውስጥ በተዘጋጀ የውይይት መድረክ ኅሣን መሠረት አድርጎ የተደራጀ የፖለቲካ ማኅበር ተወካዮች የተነሱና ኅብረ ብሔራዊ ሆኖ የተደራጀ የፖለቲካ ማኅበር ተወካዮች ባደረጉት ንግግር/ማብራሪያ ላይ ተመሥርቶ የተሠነዘሩ አስተያየቶችና አቋሞች ናቸው፡፡

በጎሣ የተደራጀው ማኅበር ተወካዮች ያነሷቸውና ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ የወሰድናቸው ዐበይት ነጥቦች ሁለት ናቸው፡፡

1ኛ/ የትግል ንጥቂያ/ሽሚያ

በዚህ ረገድ የቀረበው አስተያየት ላለፉት አራት ወራት በአዲስ አበባ መሪ ፕላን መነሻነት የኦሮሞ ጎሣዎች በሚኖሩበት የአገሪቱ ክፍል የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ዓመጽ የሚወክለው የኦሮሞን ሕዝብ ብቻ እንደሆነ አንደምታ ያለውና ሌሎች የወያኔ አገዛዝ ተቃዋሚዎች ይህንን የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ጠልፈው የራሳቸው መጠቀሚያ እንዳያደርጉት በማስጠንቀቂያ መልክ የተላለፈ መልእክት ነው፡፡ በመሠረቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል፣ በማናቸውም የኢትዮጵያ ጎሣዎች አገዛዙን ለማስወገድ የሚደረግ ሕዝባዊ እምቢተኝነትም ይሁን የትጥቅ ትግል ለአንድ ጎሣ ወይም ያንን ጎሣ ለሚወክሉ ጥቂት የፖለቲካ ቡድኖች ብቻ የሚያደርገው የሕግም ሆነ የሞራል መሠረት አለ ወይ? ወያኔ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ (ሁሉንም ጎሣዎች) አስተካክሎ አልበደለም ወይ? አገዛዙ እየፈጸመ ባለው ግፍ፣ ጭቆናና በደል ያልተነካ ኢትዮጵያዊ አለ ወይ? በውኑ የኦሮሞ ልጆች በአረመኔው ወያኔ እንደ ቅጠል ሲረግፉ ትግላቸውን መሥመር ያስያዘላቸው አለ? ኧረ ግፍ ነው ኧረ ነውር ነው በኢትዮጵያውያን ደም መቀለድ? ሕፃናትና እናቶች እየሞቱ የሥልጣን ስሌት/ቁማር ውስጥ ገብተናል ማለት ነው? ይህንን አመለካከት የሚያንፀባርቁ ቡድኖች አገራዊ ዓላማ፣ ርዕይ፣ ፖሊሲ፣ አጀንዳና መርሐግብር መገለጫው ይህ ነው ማለት ነው? ከሆነ በእጅጉ ያስደነግጣል፡፡ ይህ አስተሳሰብ በትጥቅ ትግል መሥዋዕትነት ከፍዬ የያዝኩትን ሥልጣን ማንም አይወስድብኝም፤ ኢትዮጵያን ‹በድሬም› የመግዛት መብት አለኝ ብሎ ከሚፎክረው ወያኔ በምን ይለያል? በፓርቲ ፖለቲካ እሳቤ ውስጥ የጎሣ ፖለቲካ ብዙም የማያራምደው አንዱ ምክንያት ለሁሉም በእኩልነት ለመቆም ያለመቻል፣ ስለሌላው አያገባኝም የማለት አስተሳሰብ/ ጠባብነት ይመስለኛል፡፡

2ኛ/ የጎሣም ሆነ ኅብረ ብሔራዊ የፖለቲካ ማኅበራት እውነተኛ ማንነት

በአገራችን ነግሦ በሚገኘው ወሮበላ ሥርዓት ስለ መድበለ ፓርቲም ሆነ ተቀናቃኝ የፖለቲካ ማኅበራት መናገር ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ይሆንብናል፡፡ በምድር ላይ ያለው ጽድቅ ይህ ቢሆንም ወያኔ እርጥባን ለሚጥሉለትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንዲፈነጭ ለፈቀዱለት አሳዳሪዎቹ ማስመሰያ በጠባቡ የፖለቲካ ሥነ ምህዳር (እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው በሚለው ብሂል) በአገር ውስጥም ሆነ በውጩ ዓለም የሚንቀሳቀሱ ተቀናቃኞች መኖራቸው ይታወቃል፡፡

እነዚህ በተቀናቃኝነት ጎራ የተሰለፉት ድርጅቶች ብዙዎቹ የወያኔን የአደረጃጀት ሞዴል የተከተሉ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ በውስጣቸውም ሆነ እርስ በርሳቸው መተማመን የላቸውም፡፡ ለዚህም ከራሳቸው የውስጥ ድክመት በተጨማሪ የወያኔ እጅ እንደሚኖርበትም ይታመናል፡፡ በተለይም የወያኔ አገዛዝ ላለፉት 25 ዓመታት በልዩነት ላይ አጥብቆ ስለሠራ መጠራጠሩ፣ አለመተማመኑ፣ ሥጋቱ የሚያስገርም አይደለም፡፡ እንኳን በፖሊቲካ ማኅበራቱ መካከል እኛ ተራ ዜጎችም የትኛው እውነተኛ ተቀናቃኝ የትኛው ወያኔ ጠፍጥፎ የሠራው ተቃዋሚ፤ የትኛው በእውነት ለሕዝብ ተቆርቋሪ የትኛው በአቋራጭ ሥልጣን ፈላጊ እንደሆነ ግራ ተጋብተን ነው ያለነው፡፡ ወያኔ ሲከተል በቆየውና አሁንም አጠናክሮ በቀጠለበት የዘረኝነት፣ የአፈና (መርዛማውን የ1ለ5 አደረጃጀት ልብ ይሏል)፣ የተቀነባበረ ዝርፊያ፣ የውሸት ፌዴራሊዝም (የጎሣ ባንቱስታን) እና የዚሁ ነፀብራቅ የሆነው የሞግዚት አስተዳደር፣ ባጠቃላይ ሕዝብን በአገሩ ጉዳይ የማያገባው የበዪ ተመልካች ባደረገው ፖሊሲ በሕዝቡ ዘንድ መተማመንን ፣ መደማመጥን በእጅጉ ሸርሽሯል፡፡

በጎሣ የተደራጀው በዜግነት የተደራጀውን አያምነውም፡፡ ኅብረ ብሔር/ዜግነት የሚለው ሽፋን እንጂ ቢገለጥ ‹ዐምሐራ› ነው ብሎ በድፍረት ይናገራል፡፡ እኔም በጎሣ የተደራጀሁት ሽፍንፍኔ ሲገለጥ ኦሮሞ ነኝ ይላል፡፡ እውነት በጎሣ የተደራጁት ሁሉ ኦሮሞዎች ብቻ ናቸው? በዜግነት/ኅብረ ብሔርነት የተደራጁትስ ‹ዐምሐሮች› ብቻ ናቸው? እንዴት ያለ ንቀት የተሞላበትና እጅጉን የወረደ አመለካከት ነው፡፡ የሰው ልጅ አእምሮ እንዴት እንደዚህ ይመክናል? ይህን መሰሉን አስተያየት የሰማሁት ‹ነፃው ዓለም› ከሚኖሩ ወገኖች ነው፡፡ ፈጣሪዬን የምለምነውና ተስፋ የማደርገውም እነዚህ ወገኖች

እንወክለዋለን፣ አርነት እናወጣዋለን እንደሚሉት ኢትዮጵያዊ ቁጥራቸው ብዙ እንዳይሆንና/እንደማይሆን ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሚባል ማንነት መኖሩን፣ አገራችን ደማቅ ባህል፣ትውፊት፣ ታሪክ፣ ልማድ፣ ወግ ያላቸው የበርካታ ጎሣዎች መኖሪያ መሆኗን ፣ በዜግነት ወይም በኅብረ ብሔርነት የተደራጁ (የጥንካሬውን ጉዳይ ለጊዜው ትተን) የፖለቲካ ማኅበራት መኖራቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚከትና በዚህም ታሳቢነት የተነገረ ይመስላል፡፡ በተጨማሪም የምወክለው ሕዝብ ቊጥር ከሌሎቹ ከበለጠ የሕዝብ ፈቃድና ይሁንታን ባላገኝም ተረኛ ጨቋኝ ሆኜ መግዛት አለብኝ የሚል አንደምታ ያለው ይመስላል፡፡ በውኑ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ የሚያራምዱ ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች ዕለት ዕለት እየሞተ ያለውን፣ ነፃነቱን አጥቶ የሚኖርባት አገር ወህኒ ቤት ሆናበት የሚሰቃየውን፣ በችግር አለንጋ የሚገረፈውን፣ በረሃብና በችጋር ተቆራምዶ የሚገኘውን፣ የወያኔ አገዛዝ ሰብአዊ ክብሩንና ማንነቱን ሙሉ ለሙሉ የገፈፈውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃሳብና ፍላጎት ያውቃሉ? ወይስ አገራችን ላይ በጉልበት እንደተፈራረቁ አገዛዞች ሁሉ ‹እኔ አውቅልሀለሁ› አንተ ሰጥ ለጥ ብለህ ተገዛ በሚለው አምባገነናዊ መርህ ወር ተረኝነት ሊገቡ?

ኢትዮጵያ አገራችን በወያኔ ከደረሰባት ውርደት በኋላ ሌላ ተረኛ ጨቋኝ (ከየትኛውም ጎሣ ይሁን የፖለቲካ ማኅበር) ለማስተናገድ በጭራሽ፣ በጭራሽ፣ በጭራሽ አትችልም፡፡ እንደ አገር ህልውናችን ካላከተመ በቀር (የሰይጣን ጆሮ አይስማው)፡፡ ወያኔ ከፍጥረቱም ከዓላማውም የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ፀር ነው፡፡ ዛሬ ይህ የወያኔ አቋም የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ በመሆኑም ቀን ከሌት አጥፍቶ ለመጥፋት አጥብቆ እየሠራ ነው፡፡ ይህ የጥቂት ዘረኞች ሥርዓት በ‹ማኒፌስቶው› (‹‹ሕገ መንግሥቱ››) የኢትዮጵያን ህልውና ለማጥፋት፣ ዜጎች የሚናገሩትን ቋንቋ መሠረት አድርጎ ዘር ለማጥፋትና በሰው ልጆች ላይ የጅምላ ወንጀልን ለመፈጸም እንዲሁም ቅጥ ያጣ ዝርፊያውን ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ያዋቀረው *የክልል አጥር* በኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ መሠረት ሊያደርጉት አይገባም፡፡ የችግራችን አንዱና ዋናው ምንጭ ምን ሆነና?

አንጋፋው ኢትዮጵያዊ ምሁር ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ባንድ ጽሑፋቸው እንደተናገሩት በምድር ላይ ያለ ጽድቅ (the reality on the ground) ሁሉ አሜን ብለን የምንቀበለው አይደለም፡፡ በጭራሽ ከማንቀበላቸው ጽድቆች መካከል የአገርን ህልውና፣ የሕዝቦችን አንድነትና አብሮነት ለማጥፋት በወያኔ መሠሪ ‹መሀን/ዲሶች› ሕጋዊ ሽፋን ተሰጥቶት የተዋቀረው የጎሣ ክልል/አጥር ነው፡፡ ወያኔ በፈጠረው በዚህ አጥር ምክንያት ሰላሙን ያላጣ፣ የሕዝብ እልቂት ያልተከሰተበት የአገራችን ክፍል አለ ወይ? የጎሣ መብት ‹ሻምፒዮን› ነኝ እንደሚለው ወያኔ የኢትዮጵያ መኩሪያ መድመቂያ በሆኑ ጎሣዎች ያፌዘ ንቀቱን ያሳየ ማን አለ? ለአብነት ያህል በቅርቡ በኦሞ ሸለቆ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (የሐመር፣የካሮ፣ የሙርሲ፣ የቦዲ፣ የሱሪ፣ የክዌጎ ጎሣዎች) ላይ የፈጸመውን፣ በ21ኛው ክ/ዘመን ሊታሰብ የማይችለውን፣ በእግዚአብሔር ምሳሌና መልክ የተፈጠሩ የሰው ልጆችን/ኢትዮጵያውያንን ከቀጠቀጠ በኋላ እጅና አንገታቸውን በገመድ አስሮ በዱር አራዊት ላይ እንኳ የማይደረግ አሰቃቂ ወንጀል መጥቀስ በቂ ይመስለኛል፡፡ ዘጠኙ የወያኔ የጎሣ ባንቱስታንስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘጠኝ የቁም ወህኒ ቤቶች ናቸው፡፡ ከስድሳ በላይ የሚሆኑ ጎሣዎችን አጥር ከልሎ ‹ደቡብ› ማለት ሕዝብን መናቅና ከፍተኛ የመብት ጥሰት ካልሆነ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? የዘረኝነት አጥሩን ሲከልል እና አሻንጉሊት አሽከሮቹን ሲሰይም ማንን አማከረ?

ዓላማችን ለሁላችን እኩል የሆነች በሕዝብ ፈቃድ ላይ የምትመሠረት ኢትዮጵያን ከሆነ፣ ወደፊት እንደሚመሠረተው መንግሥት ቅርፅ የአስተዳደር ክፍፍሉም (ለአስተዳደር አመቺ በሆኑ ነባራዊ መመዘኛዎች) ሁሉም ኢትዮጵያዊ (አናሳ ብዙኃን ሳይባል) በሚያፀድቀው ሕገ መንግሥት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ስለሆነም ወያኔ የፈጠረው የጎሣ ባንቱስታን/የአትድረሱብኝ አጥር በየትኛውም መመዘኛ ከግለሰብ እስከ ድርጅት የሚኖሩንን ጥያቄዎች ለመመለስም ሆነ በተለያዩ አገራዊ ርዕሰ ጉዳዮች የሚኖሩንን ልዩነቶች ወይም አለመግባባቶች ለመፍታት መሠረት ሊሆን አይችልም፡፡

ዓላማችን (ብሔራዊ ዕርቅ አውርደን፣ በታሪክ የተፈጸሙ ስህተቶች ካሉ እንዳይደገሙ ሥርዓት አበጅተን) በዜግነትም ሆነ በጎሣችን የምንደምቅባት የተከበረችና የታፈረች አንዲት ሉዐላዊት አገርን መገንባት ከሆነ፣ የአስተሳሰብ አድማሳችን ከጎሣ የዘለለ መሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም በፖለቲካ ማኅበር

(መሠረቱ ጎሣም ይሁን ዜግነት) የመደራጀቱ ፋይዳ አንድን ጎሣ ብቻ ነፃ ለማውጣት፣ የአንድን ጎሣ መብቶች ብቻ ለማስከበር ሳይሆን በአገዛዞች በተለይም በወያኔ ቁም ስቅሉን እያየ ያለው የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ ለመታደግ ይመስለኛል፡፡ ይህ አስተሳሰቤ ትክክል ከሆነ ‹‹ኦሮሚያ ‹የ› ኦሮሞ ወይም ኦሮሚያ ‹ለ› ኦሮሞ›› በሚል የቃላት ስንጠቃና ንትርክ ውስጥ መግባቱ ተገቢ ነው ወይ? በዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ መጠመዱስ ዘላቂ ፋይዳው ምንድን ነው? በአንድነት ታግለን እናስወግደዋለን የምንለው ወያኔ የፈጠረው የጎሣ ፌዴራሊዝም ወጤት አይደለም ወይ? የወያኔ የጎሣ አፓርታይድ ሥርዓት የፈጠረውን የወልቃይትና ጠገዴንስ ጉዳይ ከዚህ ጋር ምን አገናኘው? የጎንደርና የትግራይ ሕዝቦች (የጎሣ ማንነታቸው እንደተጠበቀ) ባላቸው ቅርበትና ጉርብትና ተዋልደው ተጋብተው ከብረው ደምቀው በአንድነት ለዘመናት ኖረዋል፡፡ ከውጭ ወራሪ ጋር ተፋልመው ዳር ድንበራችንን አስከብረዋል፡፡ አንዱ ወደ ሌላው ሄዶ ለመሥራት/ለመኖር ፈቃዱ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱ እንጂ የክልል አጥር አልነበረም፡፡ የጎንደር ሕዝብ ጎንደር የጎንደሬዎች ወይም ለጎንደሬዎች ብቻ ብሎ አያውቅም፣ አሁንም አላለም፡፡ ወያኔ በማኒፌስቶው ያስቀመጠውን ታላቋን የትግራይ ሪፐብሊክ የምትባል አገር ለመመሥረት ወልቃይት ጠገዴውን (ጎንደሬውን) በግድ ትግሬ ካልሆንክ ብሎ የጎሣ ማንነቱን በሽብርና በብረት ኃይል ካልቀየርክ ስለተባለ እንጂ፡፡ ትንቅንቁም ወያኔና አሽከሮቹ ለዘመናት ከኖረበት ቦታ ስላፈናቀሉት እና በሰፋሪ ስም ታጣቂ ኃይሎችን ልኮበት ማንነቱን እንዲክድ ስላስገደዱት እንጂ፡፡

ኢትዮጵያ በምትባል ሉዐላዊ አገር ውስጥ የሚጠቃለል ግዛት በሙሉ የአንድ ቡድን/ጎሣ ብቸኛ ገንዘብ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ የሚታሰበው በደቡብ አፍሪቃው የጥቂት ነጮች አፓርታይድ ሥርዓት፣ በወያኔ የጥቂት ጥቁሮች የጎሣ አፓርታይድ ሥርዓት ወይም ኢትዮጵያ በአገርነት የማትቀጥል (የሰይጣንና የወያኔ ጆሮ ይደፈንና) ከሆነ ብቻ ነው፡፡ (ወያኔም እንኳ ተፈጥሮውና ዓላማው አልፈቀደለትም እንጂ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 32 ኢትዮጵያውያን በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የመዘዋወርና የመኖር ነፃነታቸው የተከበረ እንደሆነ ይናገራል)፡፡

በሌላ በኩል (አላምንህም ግን አንድነት ለነፃነት በሚል) *በሁለት ልብ እያነክስን ለሁላችን እኩል* የምትሆን፣ ሥልጣን የሕዝብ የሆነባት፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፣ ዜጎች በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወት መስተጋብር የሚያደርጉባት፣ በአካባቢያቸውም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ በሚነሱ አገራዊ ጉዳዮች ባለቤቶች የሚሆኑባትን አገር መገንባት አስቸጋሪ ይመስለኛል፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ሆኖ አንድ ሉዐላዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚፈልገው ተፈቃቅደን የምንመሠርተው አንድነት/ኅብረት ጥንካሬን፣ የጋራ ብልጽግናን፣ዘላቂ ሰላምን እንደሚያመጣ ፤ መለያየት/መከፋፈል ደግሞ ድክመትን፣ የጋራ ውድቀትን፣ ለትውልድ የሚተርፍ ጥላቻንና ንትርክን እንደሚያስከትል ስለሚያምን ነው፡፡ ከጤናማ አእምሮ ጋር ላለ ማንም ሰው በዚህ መልኩ በሚፈጠር አንድነት ውስጥ የግለሰብንም ሆነ የቡድን መብቶችን ለማስከበር አያዳግትም፡፡ የዜግነት መብቶች መከበር ለወል (ጎሣ) መብቶች ዋስትና ነውና፡፡ አንድነት በመፈቃቀድ ላይ እስከተመሠረተ ድረስ ለምን የጎሣ መብት ተቃራኒ ተደርጎ ይታያል? አንድነትን፣ ኅብረ ብሔራዊነትን፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነትን ለ‹ዐምሐራው› ብቻ የጅምላ ገንዘቡ እንዲሆን (በሞኖፖሊ እንዲይዝ) የሰጠው ማነው? ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ማን ኢትዮጵያዊ ይሁን? ይህንን አስተሳሰብ የሚያራምዱ የጥቂት ድርጅቶች አመራሮች ወይም ያፈሯቸው ተከታዮች ካልሆኑ በስተቀር በጭራሽ የወከሉት ሕዝብ አመለካከት አይደለም፡፡ እንደዚህም ብለው ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን የሚያስተምሩ/የሚሰብኩ ካሉ እንታገለዋለን ከሚሉት ከዘረኛው ወያኔ በምን ተለዩ? ሕዝብን መናቅ ካልሆነ፡፡

በመጨረሻም ተቀናቃኝ የፖለቲካ ማኅበራት ስልታዊ ኅብረት/አንድነት ለመፍጠር በአገዛዙ ወይም እናንተ በምታራምዱት ጽንፈኛነት ምን ያህል ኢትዮጵያውያን ማለቅ አለባቸው? እባካችሁ ፕሮፌሰር/ጋሽ አለማየሁ ገ/ማርያም ባለማቋረጥ የሚያስታውሰን ‹ዝክረ ሰማዕታተ ኢትዮጵያ› መቼ ነው ትምህርት የሚሆነን? እባካችሁ እናንተም አዲስ ጉልበተኞች አትሁኑብን፡፡ ጨለማው እንዲገፍ እንጂ የገደል ጥላ ሆናችሁ አታጽኑት፡፡

አምላከ ኢትዮጵያ ልቦና ይስጣችሁ፣ ወደ ኅሊናችሁ ይመልሳችሁ፡፡ አንድነቱንና ኅብረቱን ያድለን፡፡